# ስሚ ትንሽ ተግባር ግዙፍ!! ማረት (ማህበራዊ ረድኤት ትግራይ)

# በትግራይና በኢትዮጵያ በተደረጉ እና እየተደረጉ ባሉት የፀረ ድህነት ትግሎች ውስጥ ቁልፍ ሚና ያላት የ38 አመት ጎልማሳዋ ማረት!!!

## እኔም ስለ ማረት (ማህበራዊ ረድኤት ትግራይ) ደስ ሲል!!

ክፍል አንድ

በፍስሀ ገመዳ ከአዲስ አበባ Fishageda@gmail.com

እኔ እንግዲህ የመፃፍ ልምዱም ችሎታውም የለኝም ነገር ግን ፍላጎቱ ስላለኝ እና ያለውን የወረወረ ፈሪ አይባልም የሚለውን የአገራችን ቢሂል በማበረታቻነት በመጠቀም በሀገራችን ውስጥ በፀረ ድህነት ትግል ውስጥ ቁልፍ ሚና ስለተጫወተችውና በመጫወት ስላለችው ማረት እና መሪዎችዋ በተለያዩ ማህበራዊ ሚድያዎች በአሉታም በአወንታም ሲጠቀሱ በማየቴ ደስ ብሎኝ እኔም ለመሳተፍ ወሰንኩኝ፡፡ ምክንያቱም ይህ ባህሪያዊ እና ሊለመድ የሚገባው ጉዳይ ሲሆን ለማረት አይነት ህዝባዊ ድርጅቶችም ጥንካሪያቸውን የበለጠ ለማጠናከር የጎበጠውንም ለማቃናት እና የቆሙለትን አላማ የበለጠ ለማሳካት ያግዛቸዋል ብየ አምናለሁኝ፡፡ በመሆኑም እኔም ስለማረት አስተዋፅኦና ድክመት ከማውቀው ተነስቼ የሚሰማኝን ለመፃፍ እና ለማካፈል ወሰንኩኝ እናም እኔም ስለማረት ደስ ሲል፤ ብየ ጀመርኩኝ ምክንያቱም የምታውቀውን እና የሚሰማህን ስለ ሀገር ልማት እና መሻሻል ትንሽም ብትሆን ማካፋል ያስደስታልና፡፡ ምክንያቱም ስለማያቁት ነገር እየዋሹ በይሆናል እና በግምት አንዳንዴም ትንሽ የሚያውቋትን በማጋነን እየፃፉ ህዝብ ከህዝብ ጋር ግለሰብ ከግለሰብ ጋር በማጋጨት እንዲሁም የድርጅቶችና የግለሰቦችን ስም በማጥፋት የሚደሰቱ ሰይጣናዊ አስተሳብ የተጠናወታቸው እና በዚሁም የሚደሰቱ እንኳን አሉ አደል፡፡ ለዚህ አብነት ፍለጋ ብዙ መሄድ አያስፈልገንም አመት ያልሞላው በትግራይ ህዝብ የተደረገው ዘመቻ በቂ ነው፡፡ ሌላው አብነት በዳሽን ቢራ የተደረገው የማጠልሸት ዘመቻና የደረሰው ጉዳት ነው፡፡ ማንም እንደሚያውቀው ዳሽን ቢራ የአማራው (ጥረት ድርጅት) እና የአማራ ህዝብ ብሎም የኢትዮጵያ ሀብት ነው፡፡ ነገር ግን በውሸታሞችና በብአዴን ጠላቶች እንዲሁም የኢትዮጵያ ልማት የማይፈልጉ ሀይሎች በተደረገበት ዘመቻ ዳሽን እንዳትጠጡ የትግራይ ወያኔ ነው ተብሎ ስለተዘመተበት በከፍተኛ ሁኔታ ይጠጣ የነበረው ዳሽን አሁን

በአማራው ክልል እንዳይፈለግ/እንዳይጠጣ ሁኗል ለምን ቢባል ውሸት የበላይነት ስለያዘ ነው፡፡

ስለሆነም የምንፅፋቸው ነገሮች እውነትና አገርንና ህዝብን የሚጠቅሙ ቢሆኑ ለህሊናችንም ለአገራችንም መልካም ነው እላለሁኝ፡፡ በመሰለኝ እና በግምት የግለሰቦችን እና የድርጅቶችን ሰብእናና ማንነት የሚጎዱ ነገሮች መፃፍ ከጉዳት ውጭ ጥቅም የላቸውም፡፡ ነገር ግን ሆን ብሎ ታጥቆ ለጥፋት የተሰለፈን ሀይል አላማው ለማሳካት ስለሆነ አትዋሽ ማለት ሞኝት ነው የሚሆነው ምክንያቱም አላማው ነውና ነገር ግን ደግሞ ዝም ብሎ መታየት ግን የለበትም ትክክለኛ መረጃ በመስጠት የተነዛው ውሸት መርዝ ሆኖ ህዝብ ሳያባላ አገር ሳያፈርስ ማርከሻ መድህኒት የሆነውን እውነት ለህዝቡ ማድረስ ተገቢ ነው፡፡ ለምሳሌ እነ ታማኝ በየነ በኢሳት ቴሌቪዥናቸው እና በውስጥ አርበኞቻቸው በመጠቀም የጎንደርን ኢኮኖሚ በማነቃቃት ከፍተኛ ድርሻ ያለውን ዳሽን ቢራ የወያኔ ስለሆነ እንዳትጠጡ ብለው ሰርቷል ተሳክቶላቸዋልም ምክንያቱም እንኳን ዳሽን ቢራ የህዳሴው ግደብ እንዳይሰራም የሚችሉንትን ለማድረግ ሞክሯል፡፡ ሰለሆነም በውሸት፣ በማስመስል፣ ወዘተ ለሀገር ጠቃሚ የሆኑ ተቋማት እና መሪዎቻችን (በተለይ ደግሞ ለአላማቸው የሞነከሱ ባህታውያን፣ አይከኖቻችን (icon) ) በተልካሾች ስማቸው ሲጠፋ መመልከት ጉዳቱ ለሀገርም ስለሚተረፍ ሁሉም ለእውነት፣ ለሀገሩና ለራሱ ጥቅም ሲል ዘብ ሊቆም ይገባል፡፡ ይህ ስል ግን ሌቦች፣ በማወቅ ይሁን ባለማወቅ የሚሳሳትቱን አይጠየቁ ፣አይከሰሱ፣አይቀጡ እያልኩኝ እንዳልሆነ ግንዛቤ ይያዝልኝ፡፡

እስቲ ወደ ተነሳሁበት የማረት ጉዳይ ልመልሳቹህ፡፡ ሰሞኑ ስለማረት እና መሪዎችዋ አንዳንድ ፀሀፊዎች በአይጋ ፎረም የፃፏቸውን ስመለከት ሁሌ በውስጤ የሚመላለስ ነገር ግን በጊዜና በመፃፍ አቅም እጥረት ሳልፅፍ ቆይቼ አሁን ግን የማያቸው የተዛቡ መረጃዎች እየበዙ ስለሄዱ እኔስ ለምን የማቀውን በማካፈል ህዝቡ ትክክለኛ መረጃ እንዲኖሮው የበኩሌን አላበረክትም ብየ በማሰብ  እና ሌሎች ከኔ የተሻለ ችሎታ ያላቸው ያዳብሩታል ብየ በማመንም ጭምር ነው፡፡ ትክክለኛ መረጃ ለሀገር ግንባታ ወሳኝ ነው ብየም ስለማምን ነው፡፡

እንግዲህ ሰለ ማረት ከማየታችን በፊት የትግራይ መሪዎች ምን ያህል visionary (አርቆ አሳቢ) እንደሆኑ እንመልከት፡፡ የትጥቅ ትግሉን በ1967 ጀምረው ከጠላት ነፃ የሚያወጡትን አከባቢ በልማት እና በእርዳታ እንዲሁም በጤና እንዲያግዝ ሶስት አመት

ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ማረትን በ1970 መሰረቱ፡፡ በመሆኑም ማረት ከተመሰረተች ጀምሮ ከተለያዩ አለማቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች፣አገራት እና ግለሰቦች እጅግ በርካታ ሀብት በማሰባሰብ የትግራይን ህዝብ ከእልቂትና መከራ ከመታደጓም በላይ የትግራይ ህዝብ በጦርነት ውስጥ ሆኖም አንዳንድ የልማት ስራዎች ማለትም የአፈርና ውሀ ጥበቃ ስራዎች፣ አነስተኛ መስኖ፣ ወዘተ እንዲሰራ እና አከባቢውን እንዲያለማ እገዛ ስታደርግ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ይህ እንግዲህ የትግራይ ህዝብ የትግል ታሪክ አካል በመሆኑ ታሪኩ ሲፃፍ የማረትም ተካትቶ የሚፃፍ ይሆናል ብለን እንገምት፡፡

አሁን እኔ ስለ ማረት ለማካፈል የፈለግኩት ራሴ በአካል የማውቀውን ከታማኝ ጓደኞቼ በተለያዩ ጊዚያት የሰማሁዋቸውና የተወሰኑ የማረት ስራዎችን በጉብኝት ያየሁትን እና በተለያዩ ወቅት በስራ አጋጣሚ ከአቶ ተክለወይኒ አሰፋ (የድርጅቱ የረጅም ጊዜ ዳይሬክተር በኔ እምነት ለአላማቸው ከቆረቡ ወይም ከመነኮሱ፣ ለአላማቸው ባህታውያን እና የትግራይ ህዝብ ከብዙዎች አንዱ አይከን (Icon) ብየ ከምገልፃቸው ታጋዮች አንዱ ናቸው) እና ሌሌች የድርጅቱ የበላይ ኃላፊዎች በተለያዩ ወቅቶች በስራ ምክንያት ቢሯቸው ስሄድ ስንወያይ የተገነዘብኳቸውን ነው፡፡ ስለሆነም ስለማረት በደምብ የማያቁ አንባቢያን በተለይም ወጣቶች እና አዳዲስ የህወሐት ይሁኑ የኢህአዴግ መሪዎች የተወሰነ ግንዛቤ ለማስጨበጥና የበለጠ ለማወቅ ደግሞ የደርጅቱ ሃለፊዎችና ሰራተኞች እንዲጠይቁና እንዲረዱ ለማገዝ በማሰብ ነው፡፡ አላማየ ደግሞ አንዳንዱ በጭፍን ጥላቻ አንዳንዱ ደግሞ ባለማወቅ በትግራይ ህዝብ፣ ድርጅቶች፣ መሪዎች እና ጥቅሞች ላይ የዘመቱትን የማቀውን ትክክለኛ መረጃ በመስጠት አንባቢ ትክክለኛ መረጃ እንዲያገኝ እና በሀገራችን ህዳሴ ላይ የተደቀነውን ፈተና ለማለፍ በሚደረገው ጥረት የበኩሌን አስተዋፅኦ ማበረከት ነው፡፡ ይህንን ስል አውቀው እና አቅደው እየተንቀሳቀሱ ያሉትን እመልሳለሁኝ ሳይሆን ከኢንፎርሜሽን ማጣት የሚታለሉትን ነው ምክንያቱም የኢህአዴግ መሪዎች አዘውትረው እንደሚሉት ኢንፎርሜሽን አቅም (ጉልበት)ነውና (information is power).

ስሚ ትንሽ ተግባሯ ግዙፍ!! በትግራይና በኢትዮጵያ በተደረጉ እና እየተደረጉ ባሉት የፀረ ድህነት ትግሎች ውስጥ ቅልፍ ሚና ያላት የ38 አመት ጎልማሳዋ ማረት፣ ብየ የተነሳሁት ምክንያት ስሚ በትግራይ ክልል ብቻ የተወሰነች ነገር ግን ደግሞ ለኢትዮጵያ ልማትና ህዳሴ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደረገችና እያደረገች ያለች ድርጅት ስትሆን በአለም ደረጃም ቢሆን የሚሊንየም ጎል እንዲሳኩ እንዲሁም በአለም በአየር ለውጥ ሳቢያ የሚደርሰውን

ጥፋት ለመቀነስ የሚያደርገውን ትግል (ለዚህ አብነት የአብርሀ ወአፅብሀ ቀበሌ በአለም ደረጃ ተሸላሚ መጥቀሱ በቂ ነው) የበኩሏን ከፍተኛ ሚና እየተጫወተች ያለች ስመ ትንሽ ተግባረ ብዙ ድርጅት ስለሆነች ነው፡፡ እንግዲህ እኔ የማቀውን ማረት ለትግራይ ህዝብ ብሎም ለኢትዮጵያ እና ለአለም ያበረከተቻቸውን ልጥቀስ ከኔ የተሻለ እውቀቱና የመፃፍ ልምዱ እንዲሁም ሀላፊነቱ እና ጊዜ ያላቸው ደግሞ አጠቃላይ የማረት አስተዋፅኦ ለትውልድ በመፅሀፍ መልክ ቀምረው እና ሰነደው ያቅርቡ ፡፡

## የማረት ጉልህ ተግባራት

ማረት በአብዛኛው ሰው የምትታወቀው በትጥቅ ትግል ወቅት በተለይ ደግሞ በ1977ዓ.ም የትግራይ ህዝብ በረሀብ እና እርዛት ምክንያት ተደቅኖበት የነበረውን እንደህዝብ የእልቂት ፈተና እንዲሻገርው ድልድይ ሆና ሰርታለች ይህ አኩሪ ተግባር ምንም እንኳ ከ30 አመታት በፊት የሆነ ስለሆነ የአሁኑ ወጣት ባይገነዘበውም ችግሩ በጣም ሰፊ እና አስፈሪ ጊዜ የነበረ መሆኑ በወቅቱ በወጣትነት እዴሜ ለነበርነው ምንጊዜም ከአይነ ህሊናችን የሚሰውር አይደለም፡፡ የ1977ዓ.ም ድርቅ ከአድዋ ጦርነት በፊትና በኃላ ለተከታታይ በርካታ አመታት እየተንከታከተ የመጣው የትግራይ አርሶ አደር ኢኮኖሚ ጭራሽ ባዶ እንዲሆን ያደረገው ሲሆን ህዝቡ የሚደረስለት አጥቶ በርሀብ አለንጋ እየተመታ ዋይ ዋይ እያለ የሚደርስለት ያጣበት ወቅት ነበር፡፡ ታለቁ የሚዚቃ ንጉስ ጥላሁን ገሰሰ፤

ዋይ ዋይ ሲሉ፤

የርሀብ ጉንፋን ሲስሉ፤

እያዘንከኝ በአይኔ አይቼ፤

ምን ላድርግ አለፍኳቸው ትቼ፡፡

ታላቁ የሙዚቃ ንጉስ ጥላሁን ገሰሰ በደረሰው ርሀብ እራሱ አልቅሶ የኢትዮጵያ ህዝበን ያስለቀሰበት ዜማ፡፡

በነገራችን ላይ የአለማችን ታዋቂ ሙዚቀኞችም በነ ጊሊዶፍ በመሪነት we are the world በሚለት እነሱ በሜርባት አለም እንዳህ አይነት ዘግናኝ እልቂት መደቀኑን ለአለም አብስረዋል፡፡

በ

ይህ እንግዲህ አንዱ አሳዛኝ የትግራይ ህዝብና የአከባቢው የዋግና እና የሰሜን ወሎ ህዝቦች ታሪክ ነው፡፡ አታምኑኝም ይህ ዜማ ስፅፍ እያነባሁኝ ነው ምክንያቱም በወቅቱ በርሀብ

ምክንያት ሲያልቅ የነበረው በለጋ የወጣትነት እድሜ እልቂቱ በአይነ ህሊናየ አይቻለሁና፡፡ ዘለአለማዊ ክብርና ምስጋና ይድረሰውና እራሱ ጥላሁን አልቅሶ የኢትዮጵያ ህዝብን በማስለቀስ የነበርው የርሀብ አስከፊነት ለትውልድ በሚተላለፍ መልክ በዜማው ቀምሮ አስተላልፎልናል ፡፡ እኔም ሁሌ ስለ ድርቅና ረሀብ ሳስብ የጥላሁን ዜማ በጆሮየ ያቃጭልብኛል፡፡ ምክንያቱም ዜማው ራሱ ለኔ የተዘፈነ ይመስለኛል በወቅቱ የተራቡ ሰዎች ከገጠር መጥተው እዚህም እዛም ኩርምት ብለው ሲስሉ በአይነ ህሊናየ በተወለድኩባት እና ባደኩቡት ከተማ በለጋነት እድሜ አይቻለሁና ምንም ማድረግ ስለማልችል ግን ከንፈሬን እየመጠጥኩኝ አልፋቸው ነበር፡፡ እናም አሁን ዜማው ሳስታውሰው እኖራለሁ፡፡

ዋይ ዋይ ሲሉ፤

የርሀብ ጉንፋን ሲስሉ፤

እያዘንኩኝ በአይኔ አይቼ፤

ምን ላድርግ አለፍኳቸው ትቼ፡፡

የሚገርም ዜማ ምን ዜማ ብቻ ለኔ ትልቅ መፅሀፍ ነው፡፡ ማንም ሰው ሊሰማው የሚገባ ከአሁኑ የአገራችን ሁኔታ ጋር ሊያነፃፅርበት የሚችል ሰነድ፡፡

በእርግጥ በኔ ግምት የወቅቱ መሪዎች ፍላጎታቸው ስለነበር ህዝቡ በጥይት ከሚጨርሱት በርሀብ ማለቁ ወጪ ስለሚቀንስላቸው ሳይደሰቱ አልቀሩም ምክንቱም ያ! ሁሉ እየሆነ ያለው መንግስት ባለበት አገር ነውና፡፡

ስለሆነም የማረት ሚና በጉልህ የሚታየው በዚሁ ወቅት የሰው ሂወት ለመታደግ በተደረገው ትንቅንቅ ሲሆን ድረቁ ካለፈ በኃላ ደግሞ የተሰደደው ወደ ቀየው እንዲመለስ እና ወደ ቋሚ መተዳደሪያው እንዲመለስ መነሻ ዘርና የእርሻ መሳሪያ በመስጠት አስቸጋሪው እና ፈታኝ የነበረውን ወቅት የትግራይ ህዝብ በተለይ ደግሞ አርሶ አደሩ እንዲሻገረው ድልድይ ሁና ሰርታለች፡፡ የማረት አመራርና ሰራተኞችም የተሰጣቸው የውጊያ ቀጠና ይህንኑ አደጋ መመከት ስለነበር በተገቢ መንግድ እነ ሓየሎም እና ሌሎች ጄኔራሎቻችን በተለያዩ አውደ ውጊያዎች አንፀባራቂ ድል እንደተቀዳጁ ሁሉ እነ ተክለወይኒ አሰፋ፤ እነ አባዲ ዘሞ ወዘተ የሚመሩት ማረትም በተሰጣቸው ወሳኝ ህዝብን የማዳን ትንቅንቅ ቀንና ሌሊት በመስራት

በብቃት የተሰጣቸውን ተልእኮ ተወጥተው ታሪክ የማይሽረው አንፀባራቂ ድል ተጎናፅፏል፡፡ ይህ እንግዲህ ብዙ የተባለበት ጉዳይ ስለሆነ ብዙ ለመፃፍ ሀሳቡም አቅሙም የለኝም፡፡

ማረት ለትግራይ ህዝብ ከምታደርገው እገዛ ጎን ለጎን ደግሞ በአማራው ክልል አከባቢ የሚንቀሳቀስ በትጥቅ ትግል ወቅት ERO (Ethiopian Relife Organization) በአሁኑ ወቅት አመልድ (የአማራ መልሶ መቋምና ልማት ድርጅት) የተባለ ድርጅት እንዲመሰረትና እና እንዲጠናከር ከፍተኛ ድጋፍ ያደረገች ሲሆን ይህ ድርጅት፡፡ ኢህዴን/ብአዴን ሲንቀሳቅስባቸው የነበሩ የዋግና የበለሳ አከባቢ ህዝቦችን ሲረዳ የቀየ ድርጅት ሲሆን፡፡ ደርግ ከተወገደ በኃላም በአማራ ክልል ውስጥ የሰው ሂወት ለማትረፍ ከሚደረግ የሂወት አድን ስራዎች ጀምሮ ከፍተኛ የመልሶ መቋቋም እና የዘላቂ ልማት ስራዎች በማከናወን የክለሉን ብሎም የሀገራችን ልማት በማፋጠን ላይ የሚገኝ የሀገራችን ህዳሴ ቁልፍ ተዋናኝ ድርጅት ነው፡፡

እንግዲህ አንባቢዎቹን ላላማሰልቸት ክፍል አንድን በዚህ ላብቃና በክፍል ሁለት ጽሁፌ ማረት በተለይም ራሴ በደምብ ከማውቀው የትጥቅ ትግሉ ካበቃ በኃላ ስላለው የማረት የፀረድህነት ትግል ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ታለቁ መሪ!!! መለስ ዜናዊ በአንድ ወቅት ስለትግራይ ድህነት ሲናገሩ "የመርፌ ቀዳዳ ታህል እንኳ መግብያ ቀዳዳ ያልነበርው" እንግዲህ የድህነት መጠኑ ምን ያህል አስከፊ እንደነበር መረዳት አይከብድም፡፡ ስለሆነም ይህን ችግር ለማቃለል ባለፉት አመታት የማረት አስተዋተፅኦ፣ በእርሻ ፣ በፊጥሮ ሀብት ጥበቃ፣ አዳዲስ ተክኖሎጂ በማስተዋወቅ(ቲሹ ካልቸር፣ የጠብታ መስኖ፣chain of ponds(dams)፣ በትራንስፖርት ዘርፍ እነ ትራንስ ኢትያጵያ እንዲቋቋሙ የነበራት ሚና፣ ሱዳን ውስጥ የነበረው የማረት ጋራዥ መስፍን ኢንዳስትሪያል ኢንዱስትሪ እንዲቋቋም የነበረው ሚና፣ የአበርገሌ የስጋ ፋብሪካ፣ የአዲግራት የማር ምርት ማቀነባበሪያ፣ የማይጨው ችፑድ ፋብሪካ፣ የውቅሮ ጋቢዮን ፋብሪካ የመሳሰሉትንና እና ሌሎች በሀገር ደረጃ ሰለፊፀመችው ተግባር ለምሳሌ በሁሉም ክልሎች እንደ ደደቢት ማይክሮ ፋይናንስ እዲቀቋቋሙ የነበራት ሚና ወዘተ እና ለማረት የቆረበው/የመነኮሰው/ መሪዋ ተክለወይኒ አሰፋ የማቀውን እንዲሁም ማረት ስላሉባት ተግዳረቶች እና መደረግ ሲለሚገባው በኔ አቅም እና እምነት መደረግ አለበት የምለውን ይገፎ በክፍል ሁለት አመለሳለሁኝ፡፡ በተጨማሪም አቶ ሙሉማር ኪሮስ እና ገብረሂወት ገብሩ የተባሉ ፀፊዎች በሰጡት ሀሳብ ላይ የተወሰነ ኮሜንቴን ይገፎ እቀርባለሁ አመሰግናለሁ፡፡

በተረፈ ግን ጽሁፌን በተለያየ ቀልም በመፃፍ የህፃን ልጅ ስእል አሰመስየ በማቅረቤ ይቅርታ እጠይቃለሁኝ ምናልባት በስነፅሁፍ ህግ ላይደገፍ ይችላል ለኔ ግን ትኩረት ያሻቸዋል ያልኩት ነው የተለየ ቀለም የተጠቀምኩት ፡፡